# በኢትዮጵያ ጉዳይ ይቅርታን ማን ይጠይቅ? ይቅርታስ ለምን?

ለዚህ ጽሁፍ መነሻው ባለ ግዙፍ ራዕይ የሆኑ ሁለት ወጣት ኢትዮጵያውያን ናቸው። እኒህ ወጣቶች የፖለቲካ እውቀት (ፖለቲካ ማለት በወሬ መደናቆር ሳይሆን ሳይንስም ነው ብለን ከተቀበልን) የተካኑ አይደሉም። በእድሜ ብዛት ከሚገኝ ልምድም ትምህርትን አገኙ ለማለት አይደፈርም እድሜአቸው ብዙ አይደለምና። እንዲሁ ቀና በመሆናቸው፣ የሰው ልጅ በደልና ጭቆና በምድራዊውም ይሁን በሰማያዊው አመለካከት ፍሬ ቢስ መሆኑን የተረዱ፣ የሚያውቁትንም ሆነ የማያውቁትን ወገን በእኩል ዐይን በማየት በመጀመርያ ከራስ መታረቅን ቀጥሎ ደግሞ መተሳሰብና መግባባትን እንደችሎታና ተሰጥኦአቸው ያስተማሩ ወንድሞች ናቸው። የፖለቲካ ስልጣን ላይ የማያማትሩ ከዘርና ከጎሳ በላይ ኢትዮጵያዊነት አንድ እንደሚያደርገን የተረዱ ናቸው። እኒህ እንድበረታታ ያደረጉኝ ወጣቶች አባንግ ሜቶና ቴወድሮስ ካሳሁን «ቴዲ አፍሮ» ይባላሉ።  የእኒህ ወጣቶችን ስራ ለመዘከር ሳይሆን እንደ ማበረታቻ በመውሰድ የግል እምነቴን ለማቅረብ ነው። በዚህም ሀሳቤን ከሚጋሩ ጋር ልንበረታታበት ከማይጋሩት ደግሞ ልንማማርበት ያጠፋን ይቅር እንድንባባልበት ነው። ለካስ ርዕሰ ጉዳዩም ስለ ይቅርታ ነው። በዚሁ ወደ ተነሳሁበት ልገስግስ እናንተም አብራችሁኝ ተጉዋዙ።

ይቅርታ ማለት አንድ ሰው ወይም ቡድን በተከተለው የተሳሳተ አቅጣጫ በዚያም ምክንያት ለተፈጸመው በደል  ወይም ያንን ዓላማ በመከተል በሌሎችም ለተፈጸመ ጥፋት ሀላፊነትን መውሰድ ይመስለኛል። ይህም ማለት በመጀመርያ ከራስ ህሊና መታረቅ ቀጥሎም በደል ወደደረሰበት ወገን ራስን ዝቅ ማድረግ ነው። ይቅርታ መጠየቅ የምህረት ተስፋ እንጂ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም። ተበዳዩ ይቅር የማለትም ያለማለትም መብት አለውና።ይቅርታ መጠየቅ የእውቀት አንጂ የውርደት መጀመርያ ተደርጎ መቆጠር የለበትም።  ይህ ጉዳይ ከህግ አንጻር፣ በተለይም ፍርደ ገምድሎች በሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ አላውቅም። ይህንን ጽሁፍ ልጽፍ በተነሳሁበት ወቅት የህግ እውቀት ያለውን ሰውም አልማከርኩም ስለዚህ አጥፍቻለሁ ብሎ በራሱ ስህተቱን ያመነ ሰው የመንግስት የጥቃት ኢላማ እንዳይሆን ሊያደርገው የሚችለውን መንገድ አላውቅም። አንዳንድ ወገኖች አደባባይ ወጥተው ይህን ሲናገሩ «እንግዲያውማ ከቃሊቲ አረፍ ብለህ ጥፋትህን ዘርዝር) ለሚሉ ሲሳይ ሊሆኑ ይችላሉና የምታውቁ ታግዙኛላችሁ የሚል ተስፋ አለኝ። ይቅርታ የምንጠይቀው ለነገ ላሰብነው የስልጣን መንገድ እንዲመቸን በትናንቱ ዳግም እንዳንወቀስ ብቻ ከሆነ ለይቅርታ መነሳታችን በራሱ ሌላ ጥፋት ይሆናል። ስለዚህ ይቅርታ የምንጠይቀው ለኢትዮጵያ ትንሳዔ ልንተጋ፣ ሌሎችንም ልናስተባብር ሊሆን ይገባዋል። ያኔ አይሆንም ያልነው ሁሉ ይሆን ዘንድ ግድ ነው። በነጻነት መኖር እውን እስኪሆን ድረስ በፍቅር ልንኖር ይቻለናልና።

እኔ ከሀይማኖትና ከፖለቲካ ጋር ጠብም ዝምድናም የለኝም። ማለቴ የሀይማኖት እውቀቴ ትንሽ ነው ቤተክርስትያን ሄጄ ካስቀደስኩኝ አስርተ አመታት አልፈዋል። የፖለቲካ እውቀቴ ወይም ተሳትፎዬ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም ስለዚህም አውቃለሁ ከሚሉቱ አልመደብም ለማለት ነው። የሀይማኖት ተቋማትና የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ እንደ «ሱፐር ማርኬት» ቢበረክቱም እንኳ ፍቅርን መስበክ ካቆሙ ሰነበቱ። የመስጊዱ ትምህርትም ብዙ ፅንፈኞችን እያፈራ ነው። አላውቅም የሚል አንሶ ነውና እውቀት የኮሰመነው አላዋቂነቴ ግር አይበላችሁ። ራስን አገዝፎ ማየት ለድንቁርና ወዶ ገባነት ነው። ከደሙ ንጹህ ነኝ ከማለት ግን ደም የለኝም ማለቱን እመርጣለሁ። እኔ ከተማሪዎች «ረብሻ» ጀምሮ አገር እስከተሰነጣጠቀችብትና አሁን አንድ ፊቱን መፍረስ እስከጀመረችበት ጊዜ ድረስ ለአለው ነገር በሙሉ በማድረግም ይሁን ባለማድረግ በመሳተፍም ይሁን ዳር ቆሞ በመመልከት የድርሻዬን ያበረከትኩ ነኝ እላለሁ እንደ ትውልድ። ኢትዮጵያ ከጥሩ ወደ መጥፎ ከተሸጋገረች እንደ ትውልድ በአጥፊነት እፈረጃለሁ። ማንም ስለበደለ ይቅር ይበል ከማለቴ በፊት እኔው ልቀድም ይገባል ባይ ነኝ። ያውላችሁ እንግዲህ እነ እገሌ አጠፉ እነ እገሌ አፈረሱ ከማለትና የመጀመርያውን ጠጠር ከመወርወሬ በፊት ለናንተ ጠጠሩን ተውኩላችሁ።

ሰሞኑን «እገሌ እኮ ላጠፋው እንኳ ይቅርታ አልጠየቀም» የሚሉ ሙገታዎች እሰማለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ መሀሪ ነው የሚሉ ወገኖችንም እንዲሁ። ይህ ጥያቄ ለምን ተነሳ አይደለም የኔ ችግር። ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ አጥፍቻለሁ፣ ሀገር የጠቀምኩ መስሎኝ በተሳሳተ መንገድ ሄጃለሁ ወይም በተቃራኒው ጥቅም አሳውሮኝ፣ የእውቀት ድሃ ሆኜ በደል ሰርቻለሁ ፈቃዳችሁ ከሆነ ማሩኝ አለያም ቅጣቴን ልቀበል ዝግጁ ነኝ ብሎ በርከክ ያለ ወይም አንገቱን የደፋና የተማጸነ ማን ነው እላለሁ?  በሩዋንዳ ስለደረሰው ጭፍጨፋ ሁላችንም እናውቃለን። ብዙ ተደከምበት ይቅር እየተባባሉ መኖር ጀምረዋል። ነገር ግን ቢያንስ ሁለት ውይይቶች ይታወሱኛል ቀንጨብ ላድርግላችሁ። አንድ ወጣት ዘመዶቹን ሁሉ አጥቷል። ሁሉም ነገር ጭል ጭል እያለ ነው የሚታየው ጥፋቱ ሲደርስ ህጻን ልጅ ነበርና። እናም «...ለሁቱዎች ይቅርታ አድርገህላቸዋል ወይ?» ለሚለው ጥያቄ የሰጠው መልስ «....ዘመዶችህን ገድያለሁ ይቅርታ አድርግልኝ ብሎ የጠየቀኝ የለም» ስለዚህ ይቅርታ ለማን ነው የማደርገው ብሎ መልስ ሰጠ። አንዱም ጎልማሳ ለተመሳሳይ ጥያቄ « .... እኔ ሚስቴንና ልጆቼን የገደለ ሰው መጥቶ እኔ ነኝ ቢለኝ ቢያንስ ያረፉበትን ቦታ እጠይቀዋለሁ የምይዘው ቂም አይኖረኝም። የማዝነው ሚስቴንና ልጆቼን የገደሉ ሰዎች ተጸጽተው ይቅርታ ሳይጠይቁኝ ይቅር ብለህ አብረሀቸው ኑር ሲሉኝ ነው...» ብሎ እንባውን ሊቆጣጠር አልቻለም። ስለዚህ መሀሪ ማለት ይቅር ባይነት ከሆነ ይቅር ለማለት ደግሞ ይቅርታ ጠያቂ ከሌለ አንዱ ያለሌላኛው እንዴት ሊኖሩ ይቻላቸዋል? እና የኢትዮጵያ ሕዝብ መሀሪነት በእኔው አላዋቂነት ትርጉም ስቶ ይሆን እላለሁ እውቀት ሲያጥረኝ?

ዛሬን ድረስ በፖለቲካው አውራ መንገድ ላይ የሚመላለሱ ስማቸው ከስራቸውም ገዝፎ የሚጠሩ ሰዎች አንድም ስፍራ ተሳስተን ነበር አይሉንም። ምላሱም ብዕሩም በእጃቸው ስለአለ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካ በርስትነት የያዙም ስለሚመስላቸው ክስ ሲመሰርቱ፣ ሲወነጅሉ እንጂ እንደ ትውልድ በደል እንደሰሩ ለመናገር ቀርቶ ከራሳቸው ህሊና ጋር እንኳ እርቅ የፈጠሩ አይመስልም። አንጋፋ ነን የሚሉ የፖለቲካ ሰዎቻችን ወይም ድርጅቶች በመጀመርያ ከእውቀት ጋር ጠብ እንደጫሩና ተማሪውን ከእውቀት ምሁሩን ከውይይት እንደነጠሉትና ወደ ፍርሀትና ሽብር እንደ ጨመሩት ዛሬን ድረስ የተገነዘቡ አይመስልም። ወይንም ይህ ነገር ወደ አደባባይ እንዲመጣና በእውቅትና በፍቅር እንዲሁም በጋራ ግንዛቤ ወደ እውነት ጎዳና እንድንጉዋዝ አይፈልጉም። አንዳንዶች እንዲያውም በህይወት እያሉ ይህ እውነት እንዳይወጣ ስለሚሹ የጅብ ማጅራት እንደያዘ አህያ ፖለቲካን እስከመቃብር ያሉ ይመስላል ከመጣው ጋር ሸው ሸው ሲሉ። ደርግ ሶሻሊዝም ባስከተለው ቀውስ ይወነጀላል ነገር ግን የነገር ጫፍ እንኳ ያልያዙ ምሁሮቻችን ኮሚኒዝም የፋሽን ያህል ገብቶአቸው «እንደ ሆቺ ሚኒ እንደ ቼጉ ቬራ» ብለው ራሳቸውም ባክነው ወጣት እንዳስጨፈጨፉ

አይናገሩም። ደርግ ከፈጠረው ፍርሀት በላይ ተማሪዎች እርስ በእርስ የፈጠሩት ፍርሀትና የደቦ ስራ አገራችንን ለዚህ አድርሶአል ብለው በድፍረት የእውነት ቃል አይሰጡም። እና ያኔ ተማሪዎች የነበርን ወይም የለውጥ አቀንቃኝ ምሁሮች ይቅርታ መጠየቅ ነው የሚገባን ወይንስ ሌላ ክስ ውስጥ መግባት ወይም ጨርሶ ወደዚያ ያለመመልከት?

መለስ ዜናዊ ወይም ሌሎቹ ኤርትራን እንዳስገነጠሉ አምርረን እንሞግታለን። ለዚህ አላማ ነፍጥ አንስተው ብዙ በደል የፈጸሙትን ሁሉ እናወግዛለን። ወደ ሕዝባችን ለመመለስ እየተንደረደርን ነው የሚሉትንም መጀመርያ ይቅርታ ይጠይቁን ብለን ምርር ብለን እንናገራለን። ነገር ግን እኒህ ኤርትራን ያስገነጠሉ ድርጅቶች ጡንቻቸው እንዲፈረጥም ያደረጉ የመጀመርያው «ቡስተሮች» የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደነበሩና በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ባለ ብዙ ገድል ነን የሚሉ ኢትዮጵያ ያስተማረቻቸው ወጣት ምሁሮቻችን እንደሆኑ በመናገር ይቅርታ ለመጠየቅ አደባባይ የወጣ ኢትዮጵያዊ ማየቴን ልብ አልልም። አሁን እንደሚታወቀው ማንኛውም ግለሰብ ወደ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ሲገባ ገና በ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሀምሳዎቹ ውስጥ የኤርትራን መገንጠል አምኖ ለዚህም የአቅሙን እንደሚያደርግ የቃል ውል ገብቶ ነበር መሬት ላራሹን መዘመር የሚጀምረው። ስለዚህ ሀገር በዚህ ምክንያት ከተበደለች ይቅርታ ጠያቂዎቹ ብዙ ሊሆኑም አይደል? «በሀይል በትግል ነው ነጻነት የሚገኘው» በሚል መርህ ወደ ጫካ ትግል ሸኝተን ሲገነጠሉ ጉድ ጉድ ማለቱን ምን አመጣው? ከሰላሳ አመት በፊት ድጋፋቸውን የሰጡ ምሁራን አሁን የክስ ፋይል ይዘው ጉድ ጉድ ቢሉና ይህንን ክህደት «ያ ትውልድ» እያልን ክበነው የዘሬውን ትውልድ ብናኮስሰው እያፈጀን ላለን አሮጌ ፖለቲከኞች የገነት በርንስ ማስዘጋት አይሆንም? «ስራብ አላበላኸኝም፣ አጥፍተህም ንስሃ አልገባህም» የሚሉ ቀላል ጥያቄዎችን ባንመልስ ወደ ገሃነምስ ሊጥለን አይችልም? ምናልባት በዚህ ምክንያት ይሆናል የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድም ቀን ተማሪዎች «ረበሹ» ወይም «ረብሻ አስነሱ» እንጂ ለነጻነት ታገሉ ሲል ሰምተን የማናውቀው። ስንቶቹ ይህን እውነት አደባባይ አውጥተው መጸጸታቸውን ነግረውን ይቅር ብለናቸዋል?

የመሬት ይዞታ ዛሬ ሀገራችንን ከመለስተኛ ረሀብ ወደ ሀገር አቀፍ ችጋር በተዳፈነ  ተስፋ ውስጥ እያሽጋገራት ነው። የተፈጥሮ ሀብት  ወይም በመሬት ላይ የሚደረግ 'ኢንቨስትመንትን» ያጠፋ  እርሻ ወደ ኢንዱስትሪነት እንዳያድግ ያደረገ ክፉ መንገድ ነው ብለን ዛሬን እንሞግታለን። እንደ መፍትሄም መሬት ወደ ግል ይዞታነት ሊመጣ ይገባዋል እንላለን። ነገር ግን ደርግ መሬትን ወደ ገበሬው ሳይሆን ወደ መንግስት ይዞታነት አድርጎ ከሚታገለው ባላባት በላይ የማይሞግተው መንግስት ጠቅልሎ ሲነጥቀው ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ልብ አላልንም። እልል ብለን እንደ ትልቅ ድል ተቀበልነው በአስፈጻሚነትም ዘመቻ ሄድን ስልሳ ሺህ ሆነን። ዛሬ የዚያ መዘዝ ግዑዙ መሬት ባይከዳም ለሙ አፈር ወደ ግብፅ እንዲሰደድ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጎአል።  ደኖች እንዲጨፈጨፉ ሆኖአል በተጨማሪም  የ 'biological diversity' ጥፋትን አስከትሎአል። ዛሬን ደግሞ ትልቅ የፖለቲካ መሳርያ ሆኖ ገበሬውን መንግስት በኩርማን መሬት እንዳሻው ያምሰዋል። እንደ ትውልድ ለዚህም ጥፋተኞች ነን ግን ይቅርታ አልጠየቅንም። በዚህ ምክንያት በረሀብ ሰዎች ከሞቱ መሬት ላራሹን የዘመርን በተዘዋዋሪ ጥፋት አልፈጸምንም ትላላችሁ?

በግራና በቀኝ የወጣቶች ደም ፈሶአል። 10ኛ ክፍል ያልጨረሱ ልጆች 'ስኳድ' ሆነው 'ባንዳ' የሚሉትን ገድለዋል። 10ኛ ክፍል ያልጨረሱ ልጆች ካድሬ ሆነው 'አናርኪስት' የሚሉትን ገድለዋል። እኒህን ወጣቶች በአዝማችነት የመሩት ግን አገሪቱ ምን አቅጣጫ መከተል እንዳለባት እንኳ አያውቁም ነበር። ምናልባት ዛሬም ድረስ ላያውቁ ይችላሉ። በዚህ ወፈፌነት ውስጥ ሁላችንም ጥፋተኞች ነን። ወደፊት የማንም ሰው ደም መፍሰስ እንዳይኖርበት ውይይትን ማበረታት እውቀትን ከስሜት ማስቀደም መቻል ተገቢ ነው። ሁለት ስህተት ቢደመር አንድ ትክክል ሊሆን አይችልምና ከመአቱ የተረፍን ሰዎች አስጸያፊ ታሪካችንን ወደ «Action movie» ለውጠን አዲሱን ትውልድ ወደዚያው አዙሪት ልንከተው አይገባም። ጀግንነት በእውቀት ካልታገዘ መልሶ ሊያጠፋ የሚችል መሆኑን ሳንዘነጋ ለጠፋው ሁሉ ይቅርታ ልንጠይቅበት ይገባል። ይህ ወደ ይቅር መባባልና አብሮነት ያድጋል ለዚህም ነው አባንግ Reconciliation, solidarity, unity ቴዲ አፍሮ ደግሞ 'ያስተሰርያል' ሲሉ አሜን አሜን የሚያሰኘኝ።

እኒህ ሁለት እግዚአብሄር ፍቅርን እንዲሰብኩ የቀባቸው የሚመስለኝ ፍጡሮች ሁላችንንም እንደ ትውልድ ለአጠፋነው ይቅርታ እንድንጠይቅ የበደሉንን ደግሞ ይቅር እንድንል አጥብቀው ያበረታቱናል። ቴዲን በፍቅር ድቁናው አባንግን በቅስናው ሳስባቸው ሁለቱ የፍቅር፣ የነጻነት፣ የመከባበርና የመቻቻል ቤተ መቅደሶች ይመስሉኛል። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመኖር ተስፋ ከአላት የኒህ ወጣቶች ስራ የኳስ ሜዳውን ያስውበዋል። እንደ ሀገር ባንድ ላይ መኖር ስንችል እንደ ራዕያችን በተለያየ ሀሳብ ውስጥ ተቧድነን እንጋጠማለን እንቦርቃለንም። በነጻነት የሚያስብ ደግሞ በፍቅር ሊመላለስ አይገደውም የጥላቻ በር ዝግ ነውና። ትልቅ ሀገርና ብዙ ሕዝብን ለማስተዳደር ብዙ ሀሳብና ትላልቅ ሰዎች ያስፈልጋሉና መሻት፣ ማወቅና ማግኘት የሩቅ ህልም አይሆኑብንም። እንደ ትውልዱ አባልነቴ ሀገርንና ወገንን አንገት ላስደፉ ጥፋቶች ሁሉ መስቀሌን ተሸክሜአለሁ። እንደ ትውልድ አባልነቴ ይቅርታም እለምናለሁ። በዚህ ከተስማማን ሁላችንም የሰው ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ከማየታችን በፊት በዐይናችን የተሰነቀረውን እናውጣ። ከዚያ በሁዋላ የፍትህ ሚዛን እንዳይዛባ እንጣር። የኛ በር እስኪንኳኳ ድረስ አንጠብቅ። ይቅር መባባል ባህል ሲሆን ጥፋት እያነሰ ይመጣል። የተደባበቀ ነገር ግን የስህተት ድግግሞሽን ያስከትላል። የነገር ጫፍ ለማስያዝ እንጂ በሁለት ገጽ የሶስት ትውልድን ጣጣ አንስቶ ለመጨረስ አይደለም። በጎደለው እውቀት ያለው ይሙላ። ያወቅሁ መስሎኝ የማላውቀውን ብዬም እንደሁ ይቅርታ ይደረግልኝ። ይቅርታ የሚያደርግልኝ ሰው ግን ስህተቴንም ያሳየኝ።

የወንድማችን የቴዲ አፍሮ የእንቁጣጣሽ ጣዕመ ዜማ በአካል ባያጅባችሁም በትዝታው መልካም አዲስ አመትን እመኛለሁ!! ወያኔዎችንም ነጻ እናውጣ ቢያንስ አራት ኪሎ ካሉ ለማኞች ያህል እንኳ በነጻነት ይመላለሱ የሚለው የአባንግ ጥሪም እንዲሳካለት እመኛለሁ። መጪው ዘመን የምንማማርበት፣ አውቀንም ይቅር የምንባባልበት፣ ይቅር ተባብለንም አንድ በሚያደርጉን ጉዳዮች ተባብረን ልዩነቶቻችንን አክብረን የምንኖርባትን ሀገር ህልውና የምናስከብርበት ይሁንልን።

ከዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com